ይድረስ ለኒቼ ተርጓሚ

በክርስቲያናዊ ፍልስፍና

“የኃይለኞች ፈጣሪ”

ለተባለው የአብዲሳ ደፋር መጽሐፍ የተሰጠ መልስ

@Jacobite_apologetics27

ታህሳስ 2018 ዓ.ም.

መግቢያ

በቅርቡ ሁላችንም እዚህ ሰፈር ሲዘዋወር ያየነው "የኃይለኞች ፈጣሪ" የተባለ መጽሐፍ አለ ፤ የዛሬ ወር አካባቢ መጽሐፉን አንብቤው ጸሐፊውን የተወሰኑ ጥያቄዎች ለመጠየቅ ብሞክርም ፣ ከመልሶቹ ፣ የፍሬድሪክ ኒቼን ሀሳቦች አምጥቶ ከመተርጎም ውጪ ፣ በግሉ ያደረገው የሀሳብ ፍተሻ እንዳልነበረ ስለተረዳሁ በዝምታ ለማለፍ ወሰንኩ። በግሌ ኒቼ በጥልቅ ከማከብራቸው ጸሐፊዎች አንዱ ነው ፤ እጅግ ልዩ በሆኑ እይታዎቹ ፣ የማስብበትን መንገድ በሙሉ የቀየረ ፣ ታላቅ ፈላስፋ ነው። ኢንተርኔትና ፣ መረጃ ማግኘት ፣ የማዛጋትን ያህል ቀላል በሆነበት በዚህ ዘመን ታዲያ ፣ ተገቢው እውቅና ሳይሰጠው ሀሳቦቹ ሲኮረጁና ፣ በስርዓቱ ባልተረዱት ሰዎች ሲጣመሙ ስመለከት ቁጭት ይሰማኛል። ነገር ግን ብዙ ሰዎች ፣ መጽሐፉ ላይ የግሌን ትችት እንዳቀርብበት ስለጠየቁኝና ፣ እግረ-መንገዴንም የኒቼን ትችቶች ፣ ጥንካሬና ድክመት ማየት ስለምንችል ይህንን ጽሑፍ ለመጀመር ወሰንኩ። ብዙ የሚሆኑት የመጽሐፉ ክፍሎች ፣ የጀርባ እውቀት ለመስጠት የተጻፉ ስለሆኑ ፣ እንዲሁ አልፋቸውና ፣ መሠረታዊ ትችት ለሚያቀርቡት ክፍሎች ብቻ መልስ እሰጣለሁ።

መልሶቻችን

የሰው ልጅ ተፈጥሮና እድገቱ

ተርጓሚያችን፦ "የሰው ልጅ "የወሲብ ውጤት ስለሆነ" ከሌሎች እንስሳዎች የተለየው ነኝ ብሎ ማሰብ አይችልም።"

መልስ፦ ሥነ-አመክንዮ ለወር እንኳን ያጠና ሰው በዚህ ሙግት መገረሙ አይቀርም ፤ የሰው ልጅ ከሌሎች ፍጡራን ጋር በተወሰነ ወይም በብዙ መልኩ እንኳን መመሳሰሉ ፣ እንዴት ነው ከእነዚህ እንስሳት በመሠረታዊ መልኩ የተለየ መሆኑን የሚያስከደው? የሰው ልጅን ከሁሉም "እንስሳት" ልዩ የሚያደርገው ራሱን ማየት የሚችል ፍጡር መሆኑ ነው ፤ ንቃተ ሕሊና ፣ ነፍስ ፣ አዋቂነት ወዘተ የሚሉ ስሞች ልንሰጠው እንችላለን ፤ ዙሮ ዙሮ ግን መሠረታዊ በሆነ መልኩ ከሌሎች ሕያው አካላት እንደምንለይ መካድ አይቻልም። “እንስሳ አይደለንም” ማለት መቻላችን በራሱ ከእንስሳት እንደምንለይ በቂ ማሳያ ነው።

ተርጓሚያችን፦ "ተፈጥሯዊ ያልሆነ ነገር በሙሉ የሰው ልጅ የምናብ ፈጠራ ውጤት ነው።"

መልስ፦ የሰው ልጅ ምናብና ንቃተ ሕሊና በተፈጥሮ ምክንያት የመጡ እንደሆኑ ካመንክና ፣ ነፍስ የሚባል ልዕለ-ተፈጥሯዊ አካል እንደሌለ ቅድመ ግምት ከወሰድክ ፣ እንዴት ነው የሰው ልጅ ፣ ተፈጥሯዊ ችሎታውን ተጠቅሞ የፈጠራቸውን ነገሮች ተፈጥሯዊ አይደሉም የምትለው? ይህ ስሁት ብያኔ (definition) ችግር የማያመጣ ቢመስልም ፣ በኋላ ላይ ለምትደርስበት የዞረበት ድምዳሜ መነሻህ ስለሆነ በአግባቡ ብትፈትሸው የተሻለ ነበር።

ተርጓሚያችን፦ "ለዘመናት በእውቀት ፣ ምርምርና መሳሳት ሲዳብር የነበረው የሰው ልጆች ንቃተ ሕሊና ፣ የራሱ ምናብ በፈጠረው "ከሞት በኋላ ሕይወት" የሚባል ምናባዊ ዓለም የንቃተ ሕሊናውን እድገት አስቆመው።"

መልስ፦ የዘለአለማዊ ሕይወት አስተምህሮ የሰው ልጆችን የንቃተ ሕሊና እድገት አጨናግፎታል ለማለት የሚያስችል አንዳች ማስረጃ አልጠቀስክም ፤ ስለሌለህ ማለት ነው። የሰው ልጆች ይህንን አስተምህሮ የተቀበሉት ፣ ዘለአለማዊ የሚመስለውን ንቃተ ሕሊና ከሞት ጋር ለማስታረቅ ነው እንጂ ፣ መመራመር ለማቆም አይደለም። በአንተ መሰረት ከሄድን የሰው ልጅ በዘልአለማዊ ሕይወት ካመነበት ጊዜ ጀምሮ ምንም አይነት የእውቀትና የሳይንስ እድገት ማሳየት አልነበረበትም ፤ ይሄ ደግሞ "አብዲሳ አዲስ መጽሐፍ ደረሰ" እንደሚለው አረፍተነገር ያህል ፣ እልም ያለ ውሸት ነው።

ተርጓሚያችን፦ "ሕይወትን ለማቆየት አንድ ነገር ግድ ሆነ። ሃያልነት! Will to power!"

መልስ፦ "ተፈጥሮ በሃይል ፍትጊያ ነው የምትተዳደረው" የሚለው የኒቼ ሀሳብ ፣ ራሱ ኒቼም እንደሚያምነው ተራ ትርጓሜ ብቻ ነው።[1] እንደ እስጣይኮች ተፈጥሮ በሕግጋትና ፣ እውር ፍትሐዊነት እንደምትተዳደር ፣ ወይም እንደ ዳርዊኒስቶች ፣ በመቆየት ፍላጎት (Will to survive) እንደምትገዛ መደምደም እንችላለን። እነዚህ ሁሉ ትርጓሜ ብቻ ናቸው ፤ ጽሑፍ አይደሉም። አንዱን ትርጓሜ ወስደህ እንደ ዶግማ ማቅረብህ ፣ ኒቼን ማሰደብ ስለሆነ መታረም አለብህ።

<u>የሃይማኖት አመጣጥ</u>

ተርጓሚያችን፦ "ከሃይማኖት መምጣት በፊት የሰው ልጆች ለዘመናት የኖሩበት መንገድ ከዚህ ጠንካራ ወኔ ተነስቶ የተደረገውን ሁሉ እንደ መልካም እያዩ ነበር።"

መልስ፦ በድጋሜ የኒቼን ሀሳብ በቅጡ እንዳልተረዳኸው ያሳብቃል። በሃያልነታቸው የምታደንቃቸው ፣ ሮማውያንና ግሪኮች ከአንድም ብዙ አማልክት ያመለኩ ፣ እልም ያሉ ሃይማኖተኞች እንደነበሩ አታውቅም እንዴ? "ከሃይማኖት መምጣት በፊት" ስትል ምን ማለትህ ነው? ከክርስትና በፊት ለማለት ይሆን?

ተርጓሚያችን፦ "የደካሞች የሃያልነት ጥማት ተስፋ ሲቆርጥ...ጥላቻ የሚባል ተፈጥሮ አይታው የማታውቀው ነገር ለመጀመሪያ ጊዜ ተፈጠረ።"

መልስ፦ ንቃተ ሕሊና ተፈጥሯዊ እንጂ ልዕለ-ተፈጥሯዊ አይደለም የሚል ቅድመ ግምት ይዘን ከተነሳን ፣ የደካሞች "ጥላቻም" ተፈጥሯዊ የማይሆንበት ምክንያት የለም። ጽሑፍህን ስትጀምር ፣ "የሰው ልጅ የንቃተ ሕሊና ውጤት የሆነ ነገር በሙሉ ተፈጥሯዊ አይደለም" የሚል ያልተጨበጠ ብያኔ (definition) ስለያዝክ ነው እንዲህ አይነት የዞረበት ድምዳሜ ላይ የደረስከው። ፍሬድሪክ ኒቼ በግብረገብ አያምንም ነበር ፤ ስለዚህ "ሃያል መሆን ክልክል ነው" የሚለው የደካሞች ድንጋጌ ብቻ ሳይሆን ፣ "ደካሞች እንደዚህ ማለት አይችሉም" የሚለው ድንጋጌም መሠረት እንደሌለው አስረግጦ ተናግሯል።[2] ለዚህም ነው ግብረገብ ውስጥ ሳይገባ ፣ ደካሞችን ለመተቸት እንዲያስችለው ፣ "ከንቃተ ሕሊና የሚመጣ ሁሉ ተፈጥሯዊ አይደለም" የሚል ብያኔ ይዞ የሚነሳው ፤ ይህ ደግሞ መሰረተቢስ ድንጋጌ እንደሆነ ግልጽ ነው።

ተርጓሚያችን፦ "ድል አልሆን ብሏቸው ተስፋ የቆረጡ ደካሞች ፣ ሳይደላቸው ሊሞቱ መሆኑ ቆጭቷቸው ፣ "ከሞት በኋላም ሕይወት አለ" አሉ።"

መልስ፦ በሌላ አለም ማመንን ከድክመት ጋር ማስተካከልህ ስሜት አይሰጥም። የዘልአለማዊ ሕይወት አስተምህሮ ፣ በሃያልነት በሚያምኑ የሮምና ግሪክ ሃይማኖቶች ውስጥም ያለ ዶግማ ነው። በአንጻሩ በሃያልነት የማያምኑ ቡዲስቶች ደግሞ ፣ የዘልአለማዊ ሕይወት የሚባል ነገር እንደሌለ ይሞግታሉ። ዘልአለማዊነትን በ "ደካሞች" የተፈበረከ አድርገህ ለማቅረብ መሞከርህ ፣ የታሪክ ምህይምናህን ከማሳበቅ አልፎ ፣ ሁኔታዎችን ከመጠን በላይ የማቅለል ስንፍና እንዳለብህ ያሳያል።

ተርጓሚያችን፦ "የአብርሃማዊ ሃይማኖቶች ምንጭ ዛራቱስትራ የተባለ ፐርዢያዊ ፈላስፋ ነው።"

መልስ፦ ይህ መሰረተቢስ አፈታሪክ ነው። አንዳንድ የታሪክ ምሁራን በብሉይ ኪዳንና በዞሮአስተር ትምህርቶች መሃል ብዙ መመሳሰል መኖሩን ጠቅሰው ፣ አይሁዶች ግዞት ላይ በነበሩበት ጊዜ ከዞሮአስትሪያኒዝም የቀዱት አስተምህሮ እንዳለ ቢሞግቱም ፣ የጠቀስካቸው እንደ "አንድ አምላክ ፣ ጥሩና መጥፎ ፣ ከሞት በኋላ መነሳት ፣ ገነትና ሲኦል ወዘተ" ያሉ አስተምህሮዎች ከባቢሎን ግዞት በፊት በተጻፉ እንደ መዝሙረ ዳዊትና መጽሐፈ ምሳሌ ባሉ ድርሰቶች ውስጥም ስለሚገኙ ፣ ከዞሮአስተር እንደተቀዱ መደምደም አንችልም።[3] ሲቀጥል አይሁዶችን ከእስራኤል ያጋዙት የአኬሜኒድ ሥርወ-መንግስት በሃይማኖታዊ መቻቻል ያምኑ ስለነበር ፣ አይሁዶች የእነርሱን አስተምህሮ ወደ መጽሐፍቶቻቸው ለማስገባት የሚያስገድዳቸው አካል አልነበረም። በዚህ ርዕስ ዙሪያ በዘመኑ የታሪክ ምሁራን መሃል ያለው ያልተቋጨ ሙግት እንጂ ስምምነት ስላልሆነ ፣ ይህንን ጽንሰ ሐሳብ እንደ ታሪካዊ ሀቅ አድርገህ መሞገትህ ልክ አይደለም።

ተርጓሚያችን፦ "ክርስቶስ ከሞተ በሁዋላ ለ100 አመታት የተበታተኑት ወንጌሎች ተሰብስበው .. የዛራቱስትራ እሳቤዎች እና የደቀመዛሙርቱ ወንጌሎች በሮማን ኢምፓየር ቀሳውስት ተጠንተው 4 ወንጌል ብቻ እንዲገባ አርገው ...ከክርስቶስ ሞት 400 አመት በሁዋላ አዲስ ኪዳን .. በሮማን ኢምፓየር ተዘጋጅቶ ለመሰራጨት በቃ።"

መልስ፦ የትኛው የሮም ቄስ ነው 4 ወንጌላትን መርጦ አዲስ ኪዳን ውስጥ ያስገባው? ደግሞስ ኮዴክስ ሳይናቲከስና ቫቲካነስ እንኳን ከ 320-360 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ የተጻፉ ሁነው ሳለ እንዴት ነው አንተ ከክርስቶስ ሞት ከ 400 አመት በኋላ አዲስ ኪዳን ተዘጋጀ የምትለን? በመሠረቱ አብዛኞቹ የአዲስ ኪዳን መጽሐፍት በመጀመሪያው ክፍለዘመን እንደተጻፉና እንደተሰራጩ ሁሉም የታሪክ ምሁር ይስማማል ፤ በአራተኛው ክፍለዘመን የተደረጉ ቅኖናዎች ፣ ክርስቲያኖች ይጠቀሙባቸው የነበሩትን መጽሐፍት እውቅና መስጠት ላይ ያተኮሩ እንጂ አዲስ መጽሐፍ የመጻፍ ወይም የማስተካከል ሥራ አልነበሩም። አዲስ ኪዳንም በአንድ መጽሐፍ መልክ ለመምጣት ብዙ ጊዜ የፈጀበት ፣ ብዙ እደ-ክታባትን በአንድ ላይ ለመሰብሰብ የሚያስችሉ ኮዴክሶች ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰሩት እጅግ ቆይተው ስለሆነ ነው እንጂ ፣ ምስጢራዊ ግለሰቦች ከጀርባ አዲስ ድርሰቶች እያከናወኑ ስለነበር አይደለም። "አዲስ ኪዳን በሮማን ኢምፓየር የተሰራጨው በ 400 አ.ም. ነው" የሚለው ሀሳብህ ፣ በታሪክ ምህይምና አዲስ ደረጃ ላይ እንድትደርስ ቢያደርግህም ፣ አንተ ግን በዚህ አታበቃም።

ተርጓሚያችን፦ "ከክርስቶስ ህልፈት 500 አመታት በሁዋላ የተነሳው የእስልምና አስተምህሮትም , በወቅቱ በሰፊ የሚነገሩ እና ተሰራጭተው የነበሩትን ትምርቶች እንዲሁም መሰረታዊ የዛራቱስትራ እሳቤዎች.. በራሱ እሳቤ እና ትምህርት ውስጥ በመቃኘት እና አዲስ አስተምሮቶችን በመስበክ 23 አመታት ከወሰደ በኋላ ቁርዓን ለመዘጋጀት በቃ።"

መልስ፦ እስልምና የተነሳው በ 610 አ.ም. አካባቢ ነው እንጂ በ 530 አ.ም. አይደለም። ቀላል ታሪካዊ ሃቆችን ሳታገናዝብ የጻፍከውን አፈ ታሪክ ያነበበ ሰው "እውቀት እያሯሯጠህ ነው ፤ አንተ ግን ትፈጥናለህ" የሚለውን አባባል ቢተርትብህ ማን ይፈርድበታል?

ሳይንስና ሃይማኖት

ተርጓሚው፦ "ሃይማኖቶች ሳይንስን መቋቋም ሲያቅታቸው ሳይንስን በራሱ እንደጠላት ወደ ማየት እና አለማዊ እውቀትን ጠልተው እንዲጠላ ወደማረግ ነው የገቡት"

መልስ፦ የሰው ልጅ ከውስጣዊ እምነቶቹ ጋር የማይናበቡ ግኝቶችን በፍጥነት ያለ መቀበል አባዜ አለበት። ይህ ለሶቅራጢስ ጠላቶች ፣ ለጋሌሊዮ አሳዳጆች ፣ ለክርስቶስ ሰቃዮች ወዘተ ሁሉ እውነት ነበር። መሰል ግጭቶችን በሃይማኖተኝነት ምክንያት የሚመጡ አድርጎ ማሰብ ፣ ታሪካዊ ክስተቶችን ባለማጥናት የመጣ ከመሆኑ አልፎ ፣ ሃይማኖተኛ ለነበሩት ሳይንቲስቶችና ፈላስፋዎች ራሱ ስድብ ነው። ከካቶሊክ ቤተክርስቲያን ጋር ስለተጋጨ በመጽሐፍህ ያነሳኸው ጋሌሊዮ ራሱ ፣ ስለ ሃይማኖት መጥፎነት ስታወራ ቢሰማህ ፣ በተራው በቁምህ እንድትታሰር ባደረገ ነበር።

ተርጓሚው፦ "[ተዓምራት] ማስረጃዎች የሌላቸው የፊዚክስና እና የተፈጥሮን ህጎችን የሚጥሱ ገለልተኛ አካላት ያላረጋገጡት እምነት ብቻ ናቸው።"

መልስ፦ ለተዓምራት የምንሰጠው ብያኔ/definition ፣ "የተፈጥሮን ሕግ የሚጥሱ ክስተቶች" የሚል ስለሆነ ፣ "ተዓምራት የተፈጥሮን ሕግ ስለሚጥሱ አልቀበልም" ማለት "መላጣ የሆንኩት ጸጉር ስለሌለኝ ነው" የማለት ያህል ባዶ የሆነ እውር ታውቶሎጂ ነው። የሂዩምን መሰረት የለሽ ናቹራሊዝም ተደግፈህ በ 2025 ሃይማኖተኞችን ለመተቸት መሞከርህ ፣ ትንሽ ወደ ኋላ እንደቀረህ ያሳያል። ከዘመኑ ጋር እየተጓዝክ ጃል!

ሥነመለኮት

ተርጓሚው፦ "የዚ ሁላ ዩንቨርስ ፈጣሪ እንደኛ ሁሉ የሆነ ነገር እሚፈልግ ፣ ስሜት ያለው ነገር ንደሆነ ከማየት በላይ እሚገርም ነገር አለ?"

መልስ፦ ፈጣሪን ቀናተኛ ፣ አዛኝ ፣ ተናዳጅ ወዘተ የሚሉ መግለጫዎች ስንሰጠው ፣ ለመረዳት እንዲያግዙን ምስስሎሾችን እየተጠቀምን እንጂ ፣ እንደ ሰው ልጅ ስሜቶች እንደሌሉት ግልጽ ነው። በመሠረቱ የሰው ልጅ በቋንቋም የተገደበ ከመሆኑም አንጻር ፣ እግዚአብሔርን ቀርቶ ፣ ፍጥረታትን እንኳን በቅጡ መግለጽ አይችልም። ፈጣሪ ከፍጥረታት ሁሉ ስለሚለይ ፣ ምስስሎሽ ውስጥ ሳንገባ ለመግለጽ ካሰብን ፣ ጭራሹኑ አንገልጸውም ማለት ነው።

ተርጓሚ፦ "እኔ ፈጣሪን እማስበው እንደዚ ሰፊ ልዩነት ያለው አካል አርጌ ነው ። ታዲያ የኔን ያክል ፈጣሪን በልህቀቱ ልክ ያየው ማነው?"

መልስ፦ ስለ ቋንቋ ግድብና ያወራሁትን ሀሳብ እዚህ ጋር በአሪፍ ምሳሌ ደግፈኸዋል። "እግዚአብሔር ከፍጥረታት ሁሉ ይለያል" ማለት ፣ አዲስ መረጃ የሚሰጥ የሚመስል ፣ እርባናየለሽ ሐረግ ነው። አንድ ሰው ከፊቴ ቁሞ ፣ "ከእኔ ጋር በቁመት የሚለያይ ሰው ለማሰብ ሞክር" ቢለኝ ፣ በቀላሉ አደርገዋለሁ። "በቁመትና በእድሜ" ቢለኝም እንደዚሁ። ነገር ግን "ከእኔ በሁሉም ነገር ፈጽሞ የተለየ ነገር ለማሰብ ሞክር" ቢለኝ አልቸልም። ጭንቅላታችን የሚሰራው በምስስሎሽና ፣ ሄጌሊያን ነጌሽን (Hegelian negation) ስለሆነ ፣ እግዚአብሔርን ያለ ምንም ማስተያየት ለመግለጽ መሞከር ፣ ከአየሩ ጋር እንደመጣላት ነው።

ሃይማኖትና ፍትሐዊነት

ተርጓሚ፦ "ስሜታችንን ንቃተ ህሊናችን በሕግ ተቆጣጥሮት ማሽን እንድንሆን አንፈቅድም! ሰው ነን! የሃይማኖት ማሽኖች አታርጉን!"

መልስ፦ ስሜትህን መከተል ከሆነ የምትፈልገው ለምን እንደ ሴድ ሊበርቲን ሆነህ አታርፈውም? ኒቼ "ፍልስፍና ሁሉ የፈላስፋው ኑዛዜ ነው" ይላልና እዚህ ጋር እየተናዘዝክ ይመስለኛል። እንዳንተ አይነቱ ላይ እንደውም መንግሥት ተጨማሪ ቁጥጥር ቢያደርግ ከጥንቃቄ አንጻር ሳያስፈልግ አይቀርም።

ተርጓሚ፦ "ነፃ ፍቃድ አላቹ ከተባለ በሁዋላ ... የቢሊዮኖችን ነፃነት በህግ ማሰሩ ምን ሚሉት ጨዋታ ነው ? ይሄ የፈጣሪ ነው የፖለቲካ አሰራር?"

መልስ፦ አሁንም ቢሆን በመጽሐፍህ ያነሳሃቸውን የመጠጣት ፣ የመዘሞት ወዘተ ፍላጎቶች የከለከለከህ ሕግ የለም። ነጻ ፈቃድ እንዳለህማ ይህንን እብደት በመጻፍ አሳየኸን እኮ!

ተርጓሚ፦ "የኦርቶዶክስ ገድል ላይ እቺን ነገር አንብቤ ገርማኝ ነበር .. “አንዴ ክርስቶስ ሳምራ የተባለች ሴት እግዜር እና ሰይጣንን ለማስታረቅ ተነሳች ... ከዛ እግዜር እና ሰይጣን ለእርቅ ሽምግልና ተቀመጡ እና ...በመጨረሻ እርቁ ሳይሳካ ቀረ... እርቁን አልፈልግም ያለው ማን ቢሆን ጥሩ ነው? እግዜር ፣ ይባስ ደሞ ከሁለቱም እሷ ተሸላ መገኘቷ"

መልስ፦ ሽምግልና ተቀምጠው እንደነበር እግዚአብሔርና ሰይጣን ያውቃሉ? ወይስ እነርሱም ልክ እንደኛ ከአብዲሳ ነው ለመጀመሪያ ጊዜ የሚሰሙት? የክርስቶስ ሳምራ ሰይጣንን የመመለስ ሙከራ ያልተሳካው ፣ ልታናግረው በሞከረች ጊዜ ሰይጣን ራሱ ሊያጠቃት ስለሞከረ ነው እንጂ ፣ በእግዚአብሔር እምቢተኝነት አይደለም። ገድሉን ጭራሹኑ አልከፈትከውም ወይም ጠጥተህ ነው ያነበብከው ማለት ነው።

ተርጓሚ፦ "እኔ [ሃይማኖቶች በተፈጠሩበት ዘመን] ብሆን ቢያንስ ይሄን የማስተካከያ ሃሳብ አዋጥቼ ሃይማኖቶችን ከመጥፋት አድናቸው ነበር። "ፈጣሪ ኑብስን ከሞት እያስነሳ እሚያንገላታ አካል ነው ብለን አስፈራርተናቸው ፣ ፈጣሪ መልካም ነው ፣ ብሎ መስበክም ይጋጭብናል… አሁን ያልተማረው ህዝብ ቢያምነን እንኩዋን … ወደፊት እንደ አብዲሳ አይነት ልጆች ህዝቡን ያባንኑት ይሆናል" እላቸው ነበር።"

መልስ፦ የፈጣሪን ቅጣት (ፍትሐዊነት) እንደ መልካምነቱ ማፍረሻ ለመጠቀም መሞከርህ ሳያንስ ፣ ራስህን እንደ አንዳች ነጻ አውጪ ሴጅ ማየትህ በእውነቱ አስቂኝ ነው። የአንተና የመሰሎችህ ነቢይ የሆነው ኦሾን ያነበበ ሰው ምን ያህል በኢትዮጵያ ከሚገኙ ኢአማንያን ብዙዎቹ ፣ ሃይማኖተኞችን "በእውቀታችን አሸንፈን መማረክ አለብን" የሚል ድብቅ ሕጻናዊ ምኞት (Childish Intellectual lust) እንዳላቸው ይገባዋል። አላማችሁ መማማርና ማወቅ ሳይሆን ማሸነፍ ስለሆነ ከእናንተ አይነቱ ጋር ለመወያየት መሞከር እንደ ሲሲፈስ ድንጋይ ማንከባለል ነው።

<u>ሕይወት ያለ ግብረገብ</u>

ተርጓሚ፦ "ኦፕቲሚስቲክ ኒሂሊስት ነኝ…ሂወቴ ውጣ ውረዴ ነው! ውጣ ውረዴን እወደዋለሁ!"

መልስ፦ ኦፕቲሚስቲክ ኒሂሊስት ነኝ ማለት የሚበር ጥንቸል ነኝ የማለት ያህል ስሜት የማይሰጥ አክዚሞሮን ነው። ሕይወት ትርጉም ከሌለውና የግድ በሞት የሚገባደድ ከሆነ ፣ ለምኑ ነው ኦፕቲሚስቲክ (ተስፈኛ) የሆንከው? ትርጉም የለሽ ብቻም ሳይሆን እርባናየለሽ መሆኑን እያወቅህ ውጣ ውረዴን እወደዋለሁ ከማለት የበለጠ ራስን ማታለል ያለ አይመስለኝም።

ተርጓሚ፦ "ሴቶችን እማትደፍረው 'አትድፈር' ስለተባልክ ከሆነ … አንተም ውስጥ የታሰረ ጭራቅ እንዳለ እወቅ! ሰዎች ቢሸሹህ አትፍረድባቸው"

መልስ፦ ከጅምሩም ግብረገብ የሚባል ነገር የለም ፤ ሁሉም የኛው ፈጠራ ነው ብለህ ከተነሳህ በኋላ ፣ መድፈርን የምታጣጥለው ምን ላይ ቆመህ ነው? ማህበረሰቡ አታድርግ ስላለኝ ነው የማላደርገው ካልክ ፣ ያንተ አቋም "ፈጣሪ ስላለኝ ነው የማላደርገው" ከሚለው ሰውዬ በምን ተሻለ? "የራስህን ሞራል ራስህ ቅረጽ" የሚለው ሀሳብህ በቻይንኛ "የፈለግከውን አድርግ" ማለት አይደለም? በድጋሜ ልጠይቅህ ፣ የሊበርቲኒዝም አቀኝቃኝ ከሆንክ በግልጽ ንገረን።

ተርጓሚ፦ "የግለሰቡ ሞራል ተፈጥሮውን እሚያሳጣ መሆን የለበትም"

መልስ፦ አዎ! እንደዚህ ግልጽ ስታደርገው ደስ ይላል። በእውነቱ ሴድ ደቀመዝሙሩን አገኘ! ተፈጥሯችንን መከተል ስለሆነ ያለብን ፣ መግደል ፣ መስረቅ ፣ መዘሞት ፣ መዋሸት ወዘተ ክልክል አይደሉም ማለት ነው ፤ እነዚህ ሁሉ ከተፈጥሮ የታደልናቸው እሴቶች ስለሆኑ። ከሩሶው (Rousseau) ተፈጥሮን መውደድ ተነስተህ ፣ በኒቼ ጸረ-ግብረገብ ፍልስፍና አልፈህ ፣ ኒካዬቭ ጋር እየደረስክ ነው ፤ ግፋበት!

እቅበተ-ሥጋ

ተርጓሚው፡- "ታዲያ ተፈጥሮህ አድርግ ብሎህ ... የሞራልህ ጌቶችህ አታድርግ ሲሉህ ... ያ ውስጥህ የመነጨው የተነሳሽነት ኬሚካል... በድርጊት መልክ እንዳይወጣ ሲገደብ ... መውጫ መንገድ ያጣና ... ተመልሶ ወደ አእምሮህ ይረጫል! ከዛስ... እራስህን ይበላሃል!"

መልስ፡- ምናልባት ይህንን ስትል ስለመነኩሴዎች እያወራህ ሊሆን ይችላል ፤ ነገር ግን በቁጥር አነስተኛ የሆኑ ምሳሌዎችን ይዘህ ሙሉ ክርስትናን መተቸትህ ስሜት አይሰጥም። ድርጊቱን የሚያከሩት መነኩሴዎች እንዳሉ ባይካድም ፤ የምንኩስና ኑሮ ግን ከጅምሩም በሙሉ ፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተና (ባታደርገውም ማንም አይከስህም) ሥጋን ጎድቶ መንፈስን ማጠንከር ላይ ያለመ ስለሆነ ፣ ሥጋዊ ጉዳት ማምጣቱ ያልታሰበበት አደጋ አይደለም ፤ የሞራል ጌቶች የጫኑብህም ሊሆን አይችልም። ወደ ተራው የክርስቲያን ሕዝብ ስንመጣ ፣ ከዓለማዊ ደስታ መታቀብ (Asceticism) በልኩ ሲሆን ሥጋዊም መንፈሳዊም ሰላም የሚሰጥ አኗኗር እንጂ "ራስህን የሚበላ" ድርጊት አይደለም። 90% ሀሳብህን የገለበጥክበት ኒቼ እንኳን ፣ እንደ ካንትና ሾፐንሃወር ያሉ ፈላስፋዎች ከዚህ በእጅጉ እንደተጠቀሙ አስምሮ ፣ እንደውም ዘመናዊ ሳይንስ ከእቅበተ-ስጋ የመነጨ እንደሆነ ይደመድማል።[4] አዎ! አይንህ አላታለለህም ፤ በኒቼ መሰረት ፣ ዘመናዊ ሳይንስ የመነጨው ከእቅበተ-ስጋ ነው። አንተ ራስህ እንኳን በትርጓሜ መጽሐፍህ እቅበተ-ስጋ ለ ኪነጥበብ ፣ ፍልስፍና ፣ ስነ-ስዕል ወዘተ መበራከት ትልቅ ሚና እንደነበረው አምነሃልና ፣ የክርስትና ስህተት ሰዎችን በሳይንስና በኪነጥበብ እንዲራቀቁ ማድረጉ ነው ማለት ነው? ከዚህ ባለፈ እንደ ኢፒኩረስ ያሉ ሄዶኒስቶች እንኳን የተሻለ ደስተኛ ሕይወት ለመኖር ከምግብ መጾም አንዳንዴ አስፈላጊ እንደሆነ ሞግተዋል። ዘመናዊ ሳይንስ ፣ የሚነግረንን የጾም ጥቅሞች እዚህ መዘርዘር አያስፈልገኝም። ከስጋዊ ፍላጎቶች መታቀብን ሃይማኖት እንደጫነብን ጎጂ ተግባር አድርገህ ማቅረብህ የለየለት ቅጥፊት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ የሰው ልጅ "ተፈጥሯዊ" ፍላጎቶች ሙብላትና መጠጣት ብቻ ሳይሆኑ ፣ ማታለል ፣ መስረቅ ፣ መግደል ወዘተ ጭምርንም ስለሚያጠቃልል ፣ እነዚህን ፍላጎቶችህን ስትገታ (በእርግጥ ከጽሑፍህ ይህ አጠራጣሪ ነው) ፣ አንተም "እየመነኮስክ" መሆኑን አትርሳ።

ተርጓሚ፡- "ታዲያ እራሱን የጠላ ሂወት የጠላ አለምን የጠላ ሰው ... ይሄ በግድ ታምቆ ውስጡ የኖረ የግፊት መአት ... የፊነዳ ቀን ትከክለኛ አውሬ ሆኖ ይመጣል ... ለዚህ ነው ሃይማኖተኛ ህዝቦች ጦርነት ላይ ፍፁም አውሬ እሚሆኑት። ለዚ ትግራይ ጦርነት ምስርክ ነው።"

መልስ፡- የሃይማኖተኞች ውጊያ የበለጠ አረመኔያዊ ነው ለማለት የሚያስችል ምንም ማስረጃ የለህም። በታሪክ ብዙ ሞቶች ከተመዘገቡባቸው ውጊያዎች ውስጥ ከፍተኛ ደረጃ የሚይዙት ሁለቱ የዓለም ጦርነቶች ፣ የሞንጎሎች ወረራ ፣ የቻይና እርስ በርስ ጦርነት ወዘተ በሙሉ ከሃይማኖት ጋር ምንም የማይገናኙ እልቂቶች ናቸው። ታሪካዊ ምህይምናህንስ ለምደነዋል ፣ ግን ያልገባኝ ነገር ግብረገብ የለም ብሎ የሚያምን ሰው በምን መስፈርት የሰው እልቂትን መቃወም እንደሚችል ነው። ደግሞስ "ስሜቶቻችንን ልቀቋቸው" ብለህ ከጨረስክ በኋላ ፣ የእነዚህ ስሜቶች መለቀቅ ወደ እልቂት እንዳያመራ መፍራትህ ምንን ያሳያል?

ተርጓሚ፡- "ሃይማኖት ደመነፍሳዊ ግፊቶችን ፣ እንደ ተፈጥሮአዊ ግፊትነት ሳይሆን እሚወስደው ... ጭራሽ “የተፀናወታቹ ሰይጣን አለ ... ነብሳቹ ንፁህ ብትሆን ይሄ አይሰማችሁም ነበር” ... ብሎ ለፀፀት ይዳርጋችዋል... ለተሰማቹ ሰውኛ ስሜት ብቻ ሃጥያተኝነት እንዲሰማን ይፈረድብናል ያኔ ነው ታዲያ እራሳችሁን መጥላት እምትጀምሩት"

መልስ፦ ሰይጣን አለ የሚለው አስተምህሮ ፣ ክፉ ሀሳቦች ምንጫቸው እኛ እንዳልሆንን በማስተማር እምቢ እንድንላቸው ይገፋፋናል እንጂ ራሳችንን እንድንጠላ አያደርግም። የክርስትና ዋና ትምህርት በመሠረቱ ራሳችንን ማዕከል አለማድረግ (Decentering ourselves) ላይ የተመሰረተ ስለሆነ ፣ ራስህን መውደድ ወይም ራስህን መጥላት ላይ የተመሰረተ አይደለም ፤ ክርስቶስን መውደድ እንጂ። ለኋጢአተኛነትህ እውቅና መስጠት ፣ ራስን መጥላት መስሎ ከተሰማህ ፣ ናርሲሲስቲክ ዲስኦርደር (Narcissistic disorder) ሊኖርብህ ስለሚችል ፣ ምናልባት የሥነልቦና እርዳታ ያስፈልግሃል ማለት ነው።

<u>የአብዲው ኒቼ</u>

ተርጓሚ፦ "በፍልስፍናው የአውሮፖ ቤተክርስቲያኖችን ጭር እንዲሉ ያደረጋቸው ታላቁ የዘመናችን አሳቢ ኒቼ የሞራልን ሰውሰራሽነት ብትንትኑን አውጥቶ አሳየ በመጨረሻ ሰበረው… ኒቼ ይሄን አለ… ፈጣሪ ሞቷል!"

መልስ፦ ኒቼ የአውሮፓ ቤተክርስቲያኖችን ጭር እንዲሉ ሊያደርግ ይቅርና ፣ ሲጀመርም በሕይወት እያለ ፣ ሥራዎቹ እምብዛም እውቅና አልነበራቸውም። መጽሐፍቱን ብታነብብ ኖሮ ፣ ምን ያህል የዘመኑ ሰዎች ሀሳቡን ስላልተቀበሉት ፣ እንደተበሳጨ ይገባህ ነበር። "ከእንግዲህ ለባልደረቦቼ እንጂ ለሕዝቡ አልሰብክም" ሲል የተናገረው ኒቼ ፣ ሕዝቡን በአስተምህሮው እንደቀየረ ስትናገር ቢሰማህ ምን ይላል? ሲቀጥል "ፈጣሪ ሞቷል" የሚለው የኒቼ ንግግር ፣ በክርስትና አናምንም ብለው ከክርስትና ግብረገብ ውስጥ የማይወጡ ኢአማንያንን ማንቃት ላይ ያተኮረ እንጂ ፣ ራሱ ኒቼ ያደረገው ድርጊትን የሚገልጽ አይደለም። ያው ይህንንም በወሬ ሰምተከው ነው እንጂ በቅጡ እንዳላነበብከው ግልጽ ነው።

ተርጓሚ፦ "ኒቼ የሞራልን ድልድይ ሰብሮ ብቻ ቢያበቃም ግን .. በዛ ብቻ እንዳያበቃ …'ቅደሙኝ' ብሎን ለኛ መንገዱን ከፍቶልን አልፎዋል ለዚህም ሁሌም እማከብረው ሰው ነው…ባለውም መሰረት በአዲሱ ትውልድ ፍልስፍና ኒቼ ፈጣሪ ሞቷል ብሎ ካቆመው እንቀጥል!"

መልስ፦ ኒቼ ፈጣሪ ሞቷል ብሎ አላቆመም ፤ የራሱን አዎንታዊ ፍልስፍና ቀርጾ ነው ያለፈው። ዘላለማዊ ድግግሞሽ ፣ ኡበርሜንሽ ፣ እጣፈንታን መውደድ ፣ አዲስ እሴቶችን መፍጠር ወዘተ ካስተማራቸው ሃሳቦች ይጠቀሳሉ። ይህንን እንኳን ሳታውቅ ፣ ራስህን የኒቼ ተከታይ አድርገህ ማሰብህ ለእርሱ ብቻ ሳይሆን ፣ ለፍልስፍናው አለም ያለህን ንቀት ያሳያል።

ተርጓሚ፦ "ሰው ምንድን ነው? መልሱ ይሄ ነው "ፈጣሪ" "እኛ ፈጣሪ ነን" በተፈጥሮ ታሪክ ፣ ከተፈጥሮ ውስጥ የወጣ ፈጣሪ ፣ ሰው ነው"

መልስ፦ ከኒቼ ፍልስፍና ልቀጥል ብለህ ፣ የኒቼ ፍልስፍና ውስጥ እየተንቦራጨክ ነው ወዳጄ! የራስህ ሀሳብ ከሌለህ ለምን በግልጽ አትነግረንም?

ተርጓሚ፦ "እና የሂወቴ ትርጉም መፍጠር ነው ? ትለኝ ይሆናል ሂወት እንድታጣጥማት እንጂ እንድትተረጉማት አልፈጠረችህም ሂወት ትርጉም እና ምክንያት እምትጠየቅ ነገር አደለችም"

መልስ፦ አሁንም የኒቼን ሀሳብ እንደራስህ አድርገህ እያቀረብክ ቢሆንም ፣ እርሱን ወደ ጎን እንተወውና ፣ በአንተ መሰረት የሕይወትን ትርጉም የሚጠይቀው የሰው ልጅ ራሱ የተፈጥሮ አካል አይደለም እንዴ? የሰዎችን ተፈጥሮ ማፈን የለብንም ካልክ በኋላ ተመልሰህ ፣ "ሕይወት ትርጉም አትጠየቅም" ማለትህ የሰዎችን ተፈጥሮ ማፈን አይሆንብህም? ሕይወት ትርጉም እንደሌላት ደርሼበታለሁ እያልክ ከሆነ ደግሞ እንደዚህ እርግጠኛ እንድትሆን ያደረገህ ምን እንደሆነ ማስረዳት ግድ ይላል።

ተርጓሚ፦ "ፈጣሪ ስራው መፍጠር ብቻ ነው። እሚጠነቀቅለት ነገር አንድ ብቻ ነው ... የፈጣሪነት ተፈጥሮውን እንዳያጣ!"

መልስ፦ ፈጣሪነቴን ባጣስ? መብቴ አይደለም እንዴ? ወይስ አሁንም ከግብረገብ ውስጥ አልወጣህም? እዚህ ጋር አንድ ታሪክ አስታወስክኝ። ኒቼ አንድ ሰሞን በከባድ ሕመም ይሰቃይ የነበረ ቢሆንም ፣ ዶክተሮች ጋር መሄድ አልፈለገም ነበርና ፣ ለራሱ በራሱ የመድኃኒት ማዘዣ ጽፎ “ዶክተር ኒቼ” ብሎ በመፈረም ፋርማሲስቶችን ይሸውድ እንደነበር የሕይወት ታሪኩ ይነግረናል። “ትዕዛዛት መኖር የለባቸውም” ይል የነበረው ኒቼ ፣ በድብቅ ሲያዝዝ የነበረው ታዲያ የመድኃኒት ማዘዣዎች ብቻ ሳይሆን ፣ የግብረገብ ትዕዛዛትም ጭምር ነው ፤ “ፍጹም ግብረገብ መኖር የለበትም” የሚለው ድንጋጌ ራሱ ፤ ግብረገብ ስለሆነ ማለት ነው። አንተም በተመሳሳይ ፣ ገላጭ (descriptive) ቋንቋ እየተጠቀምክ ፣ ፈጣሪ መሆንን እንደ ፍጹም ግዴታ አድርገህ ለማቅረብ እየሞከርክ ይመስላል። “አይ የሰዎች ተፈጥሮ መፍጠር ስለሆነ እንዲሁ እሱን እየገለጽኩ ነው” እያልክ ከሆነ ደግሞ ፣ ሰዎች ተፈጥሯቸውን already እየተከተሉ ስለሆነ ፣ መጽሐፍህ አላማ የለውም ማለት ነው።

ተርጓሚ፦ "እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ , በሂወት እያለው ኢትዮጵያ ከቻይና በልጣ ማየት ህልሜ ነው"

መልስ፦ የኒቼ ተተኪ ለመሆን የተነሳው ሰውዬ ስለ ሀገር ፍቅር እየዘላበደ ነው ቢሉ ማን ያምናል? ብሔርተኝነትን ስለናቀ የጀርመን ዜግነቱን በፈቃደኝነት አስረክቦ ፣ ስዊዘርላንድ የገባው ኒቼ ፣ የእርሱ ተተኪ ተብዬዎች ፣ አሁንም ስለ ሀገር ፍቅር የሚያወሩ የ "መንጋ አሳቢዎች" እንደሆኑ ቢሰማ ፣ መቃብር ውስጥ አይገለባበጥም?

ማጠቢያጀ

ተርጓሚ፦ "እምነት እሚከተል ሳይሆን እውቀት እሚቀድም ትውልድ ማየት እመኛለው"

መልስ፦ እርሱ ካንተ ቢጀምር የተሻለ ነበር።

ተርጓሚ፦ "ሂወቱ ከሞት በሁዋላ እንደሆነ እሚያምን ህዝብ ተይዞ ትኖውን ስልጣኔ ነው መገንባት እሚቻለው?"

መልስ፡- የግሪክ ፣ የፋርስ ፣ የሮም ፣ የአክሱም ፣ የዛግዌ ፣ የናፖሊዮን ፣ የብሪታንያ ፣ የስፔን ፣ የፖርቹጋል ወዘተ...እነዚህ ሁሉ በሃይማኖተኛ ሕዝቦች የተሰሩ ስልጣኔዎች ናቸው ፤ አንተ ስለማታውቃቸው የሉም ማለት አይደለም።

ተርጓሚ፡- "ከሞት በሁዋላ ያለውን አለም እሚመኙ ፣ ሲታመሙ ሳይንስ እግር ስር ወድቀው አድነን እሚሉት ለምን ይሆን?"

መልስ፡- አማኞችና ግብረገባውያን ራሳቸው የፈጠሩትን ሳይንስ ተጠቅመው መዳናቸው ነው የሚያሳፍረው ወይስ በፈጠሩልህ መድሃኒት ከዳንክ በኋላ እነርሱን ማብጠልጠልህ?

ተርጓሚ፡- "እቺን ነገር አንብቤ በሳቅ ሞትኩ " ዝንጀሮ የያዝከውን ሙዝ ስጠኝ እና ከሞትክ በሁዋላ ብዙ ሙዝ ይሰጥሃል ቢባል አይሰጥም ፣ ሰው ግን ይሰጣል"

መልስ፡- ስለዚህ አርቆ የማሰብ ችሎታዬ ፣ ከዝንጀሮ እኩል ነው እያልከን ነው? አሁን የጻፍከው ጀርገን ስሜት ይሰጣል¡

References

[1] Nietzsche, F. Beyond good and evil. Aphorism 22.

[2] Ibid. Aphorism 188.

[3] Basile, C. 2021. Zoroastrian influence on Old Testament Monotheism and Eschatology? A Scriptural and Sociological analysis.

[4] Nietzsche, F. On Genealogy of morals.